# “ሂውማን ራይትስ ዎች” – ፀረ-ኢትዮጵያዊነት የማይታክተው ተቋም

ቶሎሳ ኡርጌሳ

Utolosa@yahoo.com

የዓለም ባንክ ከመሰንበቻው ስድስት መቶ ሚሊዩን የአሜሪካ ዶላር ብድር ለኢትዮጵያ ፈቅዷል፡፡ በቀጣይም አብሮ ለመስራት ወስኗል፡፡ ይህ ታላቅ ድል ነው፡፡ የዚህ ግዙፍ ዓለም አቀፋዊ የገንዘብ ተቋም ውሣኔ የተሻለች ኢትዮጵያን ለምንናፍቅ ዜጎች ሁሉ በእርግጥም ድልም ተስፋም ነው፡፡

መደጋገፍ በምድራዊውም ይሁን በሰማያዊው ዕይታ እሙን በመሆኑ ቅቡል ነው፡፡ ልማታዊና ዲፕሎማሲያዊ ፋይዳውም የዚያኑ ያህል የበዛ ነው፡፡ ግና ተቋሙ ያለ አንዳች አሳማኝና በጎ ምክንያት እጁ አልተፈታምና እንድምታውም ከፍ ያለ ነው፡፡

አንድም የገንዘብ ተቋሙም ይሁን ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሀገራችን እያስመዘገበች ባለው ፈርጀ ብዙ ልማታዊ ዕድገታችንን ማመኑና መገንዘቡ ሲሆን፤ ሁለትም ገንዘቡን በተጨባጭ ለሚታይ ልማት ማዋል የሚችል፣ ኃላፊነት የሚሰማው መንግስትና ህዝብ እንዳሉ ማረጋገጡን የሚያመላክት ነው፡፡

በእርግጥ ለጽሁፌ መነሻ ይሆን ዘንድ የዓለም ባንክን በመነሻነት መረጥኩት እንጂ፤ የኢትዮጵያን ልማት ለማስቀጠል ከጎናችን የተሰለፉ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ግለሰቦች አያሌ ናቸው – የልማታችን አጋር የሆኑ መንግሥታትም ሳይዘነጉ።

ለአብነት ያህልም የአፍሪካ ልማት ባንክና ይህን ፅሁፍ በማጠናቅርበት ወቅት የኢትዮጵያን የልማት ኢንዱስትሪ ለመደገፍ ቃል የገባውን የአውሮፓ ህብረት ማውሳት በቂ ነው፡፡

የረጅም ጊዜ ወዳጃችን ቻይናም ከታንዛኒያና ከጋና ጋር የምንጋራውን አምስት መቶ ሚሊዩን የአሜሪካ ዶላር ለመስጠት ቃል ገብታለች– ታላቁ መሪያችን አቶ መለስ በተገኙበት የቡድን 8 ጉባኤ በወሰነው መሠረት።

ይሁን እንጂ በውሳኔው በተለይም የዓለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ ሀገራችን የጀመረችውን የልማት ሥራ ወደ ፊት የሚያሽከረክር ትልቅ አቅም ማግኘቷ እንደ አባጨጓሬ የኮሰኮሣቸው ግለሰቦችና ተቋማት አልታጡም፡፡

በይፋም ውግዘ ከመአርዩስ እያሉ ነው፡፡ ምንም እንኳን መንፈራገባቸው ከመላላጥ ወዲያ ምንም እንደ ማይፈይድላቸው የተገነዘቡት ባይሆንም፡፡

የዚህ ሰናይ ምግባር  ግንባር ቀደም ተቃዋሚ ደግሞ ራሱን “ሂውማን ራይትስ ዎች”  እያለ የሚጠራው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነኝ ባይ ድርጅት ነው፡፡

እርግጥ ይህ ከስሙ ጋር የማይጣጣም ስያሜን ይዞ የሚንገላወጀው ተቋም በፀረ- ኢትዮጵያነት ምግባሩ የታወቀ በመሆኑ ለውድ አንባቢዎቼ እንግዳ እንደማይሆን እገምታለሁ— ነገሩ “የወጋ ቢረሣ የተወጋ አይረሣም” እንዲል በመሆኑ።

ታዲያ ይህ ልማደኛ ተቋም በክፋት አፈ-ቀላጤው ቤን ራውለንስ አማካኝነት “አዲስ ነገር የለም” ባለው አሉባልታው መሳይ ፅሑፉ የዓለም ባንክን ምግባር አብጠልጥሏል፡፡ ዓለም ባንክን ብቻ ሳይሆን ከእኛ ጋር ወዳጅ ናቸው ብሎ የገመታቸውን ሁሉ አይናችሁን ላፈር  ብሏል –ያለ አንዳች ይሉኝታና ሃፍረት በይፋ፡፡

እርግጥ የፅሁፌ ማጠንጠኛ ከምግባሩ ጋር የማይገናኘውን መጠሪያ ጀርባው ላይ ለጥፎ የሚዞረው እንዲሁም “ለምን ታድጋላችሁ፣ትበለፅጋላችሁ” እያለ የሚከራከረው አክራሪ ኒዩ-ሊበራል  ተቋምና አገልጋዩን ቤን ራውለንስን አስቀደምኩ እንጂ፤ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፖርቲ ጭምብል አጥልቀው በጥፋት ጥምረት የተወዳጁ  “አውርቶ-በልቶ አደር” ግለሰቦችና ፓርቲዎች በደጀንነት አብረውት እንደቆሙ ከማንኛውም ሀገር ወዳድ ዜጋ የተሰወረ አይደለም፡፡

አዎ! አሜሪካ ተቀምጠው የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ነባራዊ ሃቅ ማይረዱ እንዲያው በስማ በለው፤ አሊያም አውቀው በድፍረት ብቻ ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያን ከሚያብጠለጥሉ ቆርጦ ቀጥል “ዶክተር ኢኮኖሚስት” እስከ ከአንገት በላይ ህዝቡን እንወክላለን የሚሉ የሀገር ውስጥ ተቃዋሚ ተብዬዎች ድረስ በአክራሪው ኒዩ- ሊበራል ተቋም አጨብጫቢነት ማንነታቸው የምናውቃቸው ናቸው።

ታዲያ የባህር ማዶ አውደልዳይ የውሸት ቋቶችንና የሀገር ውስጥ “አውርቶ-በልቶ አደር” ባንዳዎችን ለዛሬው በይደር አቆይቼ ወደ ቤን ራውለንስ ኢ-ሰብዓዊ አሉባልታ ልመለስ፡፡…

ቤን ራውለንስ በአክራሪው ኒዩ- ሊበራል ተቋም የአፍሪካ ጉዳይ ከፍተኛ ተመራማሪ ነኝ ባይ ነው። ይቅርታ! በፅሑፉ ላይ ተመራማሪ ነኝ ያለው እርሱው እንጂ እኔ አይደለሁም፡፡ እኔ እንኳን ኢትዮጵያዊ ጨዋነት እንዳይጐድለኝ ሰግቼ እንጂ፤ ከተመራማሪነት ይልቅ “አማራሪነት” የሚለው ስያሜ ይመጥነዋል ባይ ነኝ፡፡

እርግጥም በስም እንጂ በምግባር ተመራማሪ አይደለም፡፡ ተመራማሪነት እማሬያዊ ልብሱ ነው፡፡ እውነተኛ ማንነቱን ለመረዳት የምትሹ ካላችሁ ቤን ራውለንስ የኒዮ- ሊብራሊዝም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሥራች የሆነውና የባለ ረብጣው የጆርጅ ሶሮስ የጡት ልጅ ነው – ርዕዩተ ዓለሙን እንዲያጠምቅለት ወደ አፍሪካ የላከው ደቀ- መዝሙሩ፡፡

ታዲያ ለአራት ዓመታት ያህል ኢትዮጵን እንዳጠናት የተመፃደቀው “ጠቢቡ” ራውለንስ የዓለም ባንክ ውሣኔ “ቀሽምነትን” ለማጋለጥ ቅንጣት ያህል አላቅማማም። እንግዲህ ልብ በሉኝ የቤን ራውለንስ ጥናት የተመሠረተው በአሉባልታና በትርጁማን በኩል በፈረንካ ባሰባሰባቸው ቃለ- መጠይቆችና ምልክታዎች ነው፡፡ እሱ እራሱ የባንኩን ውሣኔ ባብጠለጠለበት ሪፖርቱ እንደ መሰከረው የመረጃ ምንጮቹ ግልብ ናቸው፡፡

በመሠረቱ የዓለም ባንክ ለኢትዮጵያ ድጋፍም ይሁን ብድር ለመስጠት የተነሳው ድንገት ነሽጦት አይደለም፡፡ እንደ እነ ጆርጅ ሶሮስ ገንዘብ የተረፈው አባ ዘራፍ ስለሆነም አይደለም፡፡ ይልቁንም በጥንቃቄ አጥንቶና አጤኖ ነው፡፡

በራሱ መለኪያ ሲመዘን የኢትዮጵያ የልማት ነባራዊ ሁኔታ ሚዛን ደፍቶ ስላገኘው ብሎም ሃላፊነት የሚሰማው መንግሥት መኖሩን ስለተረዳ በተግባር ውጤታማ መሆን በመጀመራችን “ወፌ ቆመች” ማለቱ ነው፡፡

ይህም በሀገራችን በተጨባጭ በሚታዩ የልማት ሥራዎች መኖራቸውን በራሱ የዳሰሳ ጥናት በማረጋገጡ እንዲሁም ኢትዩጵያ ተስፋ ሰጪ ሀገር መሆኗን በመረዳቱ ብሎም እጅና ጓንት፣ ደምና ሥጋ

የሆነ ህዝብና መንግስት መፈጠሩን እንዲሁም አስተማማኝ ስርዓት መገንባቱን በማስተዋሉ እንጂ ኢትዮጵያዊ አጕትና አክስት ያለው የኢኮኖሚ ጠበብት ዓለም ባንክ ውስጥ ስላለ አይደለም፡፡

በእርግጥ ሚስተር ራውለንስ እውነታውን ዘንግቶት አይመስለኝም። የኒዮ-ሊበራሊዝም ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ጋርዮሻዊ ዕውቀት ቀልቡን ካልነጠቀው በስተቀር ኢትዮጵያ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋት ብቻ ማይሆን፣ መዘግየቱንም ያውቃል– ቢያንስ በልቦናው፡፡

ግና ነገሩ “የዳቦ” ጉዳይ ሆኖበት እንጂ የዓለም ባንክን ውሳኔ ባልተቃወመ ነበር፡፡ ይሁንና ግለሰቡ ጥቂር ህዝብ በሚናገረው ሁሉ እንደማይታመን የሚያምን ትምክህተኛ በመሆኑ፣ ቢያንስ ስለ መለወጥና ስለ ማደጋችን እኛ የምንሰጠውን እማኝነት መቀበል ከተሳነው እንኳን ታላላቅ የዓለም መገናኛ ብዙሃን ኢትዮጵያ በእድገት ጕዳና ላይ በመሆኗን እንዲሁም ድጋፍና እገዛ እንደሚያስፈልጋት ሲመሰክሩ እየሰማና እያየ የሞኝ ትችት መሰንዘር ባልተገባው ነበር፡፡

ባያዝነው የአውሮፓውያን ዓመት ብቻ ከ10 ጊዜያት በላይ የኢትዮጵያን ሁለገብ ዕድገት የዘገበው የዓለማችን ተነባቢ የኒዩ-ሊበራል መጽሔትን /ዘ ኢኮኖሚስትን/ ሳያስተውል እንዳልቀረ እገምታለሁ፡፡

እኔ ግን የራሱ ጉዳይ ብያለሁ፡፡ “እያውቅምና ይቅር ይበለው” ግን አልልም– አውቆ ስለተኛ እንጂ ዓይኑም ሆነ ጆሮው ሁሉን ያስረዱታል፡፡ ግና ያው የርዕዮተ-ዓለም ነገር ሆኖበት በልቦናው እንጅ በአንደበቱ ለመመስከር ድፍረት አይኖረውም፡፡

እናም በሰብአዊ መብት ስም ተደራጅቶ የአፍሪካዊያንንና የታዳጊ ህዝቦችን አንጡራ ሐብት ለመቦጥቦጥ የላኩትን ግለሰቦች ያስቀድማል፡፡ በኒዮ- ሊብራሊስቶች እጅ ሶስት መቶ ስልሳ ዲግሪ የሚዞወር አፍሪካዊ መሪ  በየቤተ- መንግሥቱ እንዲቀመጥ ይታገላል፡፡

ግና ዛሬ ላይ ሁሉን ነገር በተገነዘበችው አፍሪካ እንዲህ ያለው ከንቱ ህልም ቅዠት መሆኑን ገና አልገባውም፣ ቢገባውም ደንታው አይደለም፡፡

“ጋርዮሻዊ አስተሳሰብ” በግልጽ አነጋገር ሲተረጎም እነ “ሂውማን ራይትስ ዎች” ሃብታሞች የድሃ ህዝቦችን ግዙፍ ሃብት ለመዝረፍ እንዲያስችላቸው በማርና በወተት ያማደጉት የርዕዮተ ዓለም ተፋላሚያቸው ነው– ዛሬ ላይ ቢሸመገልም፡፡

እናም በድፍን አፍሪካ ተሰማርቶ በሰብአዊ መብት ስም የኒዮ-ሊበራሊዝም ፖለቲካዊ- ኢኮኖሚ ፍልስፍና የሚስፋፋበትን አክራሪነት ይሰብካል፡፡ አልጠመዘዝ ያሉትን ደግሞ በሪፖርት ጋጋታ ያወግዛል፡፡ ሰብአዊ መብት እየጣሱ ነውና ይጠፈሩ፣ ይወገሩ እያለ የቁራ ጩኸቱን ያሰማል፡፡

በመሠረቱ ኒዮ-ሊበራሊዝም ጋርዮሻዊ ሥርዓት ነው፡፡ ቀደም ባሉት ዘመናት የነበረ፣ ግና ነገረ ስራው ሁሉ ከዘመኑ ዓለም ጋር የሚጣጣም ያልሆነ፡፡ ዋነኛ ዓላማው ጥቂት ግለሰቦችን በማበልፀግ ብዙሃኑን የበይ ተመልካች የሚያደርግ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

ራሱን በራሱ መብላቱን በፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ አረጋግጧል። አቅመ-ቢስና ለዜጎቹ ምንም የማይሰራ መንግስት እንዲፈጠር ልቅ የገበያ ስርዓትን የሚሰብክ ነው፡፡  ታዲያ ኢትዮጵያን የመሳሰሉ ታዳጊ ሀገራት ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ፖለቲካዊ-ኢኖሚያዊ ስርዓትን ስለዘረጉ ለኒዩ- ሊበራሊዝም ልቅ እሳቤ በራቸው ዝግ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

እናም ኢትዮጵያና መሰል የአፍሪካ ሃገራትን ከ“ሂውማን ራይትስ ዎች” እና ከአክራሪ ኒዮ-ሊበራሊዝም የፖለቲካዊ- ኢኮኖሚ አስከባሪዎች ጋር  የሚያላትማቸው ዋነኛው ምክንያት ይህንኑ መንገድ በመከተል ለባህር ማዶ ጫና አለመበገራቸው ነው።

አንዘረፍም፣ አንበዘበዝም እንዲሁም ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አንበገርም ማለታቸው ነው፡፡ በውስጥ ጉዳችን ወሳኙ የስልጣኑ ባለቤት የሆነው ህዝባችን እንጂ እናንተ አይደላችሁም በማለታቸው ነው።

ሀገራችን የዚሁ ነባራዊ ሃቅ ተጠቂ ነች፡፡ እናም “የሂውማን ራይትስ ዎች” አቀንቃኙ የቤን ራውለንስ ሰሞነኛ ፉከራም የዚሁ አስተሳሰብ ቅጥያ መሆኑ አያጠያይቅም። የዓለም ባንክ ለኢትዮጵያ ድጋፍ በማድረጉ መበሳጨቱም ሀገራችን እርሱ እንዳለው እየፈረሰች ያለች ሃገር ስለሆነች አይደለም፡፡

ከዚህ ይልቅ ሀገራችን በፌዴራላዊ ስርዓት አንድነቷን አስጠብቃ ዓለም ያረጋገጠው ፈጣን ኢኮኖሚ ባለቤትመሆኗ ነው-ዕውነታው። መቼም የአክራሪው ተቋም ነገር በግልባጩ የሚያወራ በመሆኑ ከጥላቻ ነኸርነት ውጭ ከቶ ምን ይባል ይሆን?...

ለማንኛውም የቤን ራውለንስ ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ምልከታዬ ቀጥሏል፡፡ ተመራማሪ ነኝ ባዩ ግለሰብ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ምነባንቡን እንዲህ ሲል በጣቃ መልክ ይተረትረዋል– የዓለም ባንክ ድጋፍ ህገ-ወጥ መሆኑንና አውግቶ ሲያበቃ የፖለቲካ ምህዳሩ መጥበቡን በማስከተል፡፡

በእኔ ዕይታ ምናልባትም ባንኩ ራሱን እንዲፈትሽ ምልጃ ቢጤም ሳይሞክር የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ባንኩ ዕውነታውን ስለሚያውቅ በአማላጅም ቢሆን ሊቀበለው የሚችልበት አንዳችም ምክንያት የለውም።

እኔ የምለው፣ የፖለቲካ ምህዳሩ የጠበባቸው የትኞቹ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፖርቲዎች ይሆኑ?– በግሌ እስከሚገባኝ ድረስ ሰውዬው ስለእነማን እንደሚያወራ ግልፅ አይደለም። ኧረ እሱም የገባው አይመስለኝም፡፡

እንደ ፈንድሻ ቆሎ ራሳቸውን በራሳቸው እየቆሉ ወደ ባህር ማዶ የሚበታተኑትን ግለሰቦች ማለቱ ከሆነ እርግጥም ይህ ንቀት ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም የሀገራችን ህዝብ ከጠላት ጋር ላበሩ ወፍ ዘራሽ ፖለቲከኞች የሚሆን አንዳችም ቦታ ስለሌለው ነው።

እናም ቤን ላውረንስ የክረምት ጀምበር ይመስል አሉ ሲባሉ ድንገት እልም የሚሉ አማተር ፖለቲከኞችን ሰበብ አስባብ አድርጐ ዙሪያ ጥምጥም ከመጓዝ ኢትዮጵያ የኒዮ-ሊበራሊዝምን ርዕዩት ባለመቀበሏ ደስተኛ እንዳልሆነና በጠላትነት ጭምር እንደሚፈልጋት እንቅጩን ቢናገር መልካም ይመስለኛል፡፡ ጥልም ቢሆን እኮ በወጉ ሲሆን ያምራል፡፡

ለእኔ የማይታዩ ምናልባትም ለቤን ራውለንስ የተገለጡ የፖለቲካ አማልእክቶች ከሌሉ በስተቀር እስኪሚገባኝ ድረስ በኢትዮጵያ ለአቅመ- ተቃዋሚነት የደረሱ ፖለቲከኞች የሉም፡፡ ቢኖሩም ረብ የለሽ ናቸው፡፡

እነዚያ (ስማቸውን የክርስትና አባታቸው ሚስተር ላውረንስ ይጥራቸውና) እርስ በርሳቸው የሚቧቀሱት ከሆኑም እንኳንስ ሀገርን ቤተሰብን ስለ መምራታቸው ማንም ሰው እርግጠኛ ሊሆን አይችልም– “የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል” እንዲል የሀገራችን ሰው፡፡

እዚህ ላይ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንዲገነዘብልኝ የምፈልገው አንድ ዕውነታ አለ። ይህን የምለው ኢህአዴግ አሊያም የኢህአዴግ ደጋፊ ስለሆንኩ አይደለም፡፡ ለነገሩ እውነትን ለመመስከር ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው፡፡

ኢህአዴግ ያልሆንኩት የኢህአዴግ መስመር የማያሳምነኝ ሆኖ ሣይሆን፣ ኢህአዴግነትን ስለማልመጥን ነው፡፡ የምር የታላላቆች /የእነ አቶ መለስ/ ፓርቲ ነውና እንደሚበዛብኝ ብናገር አጋነንክ የሚለኝ አይኖርም– ከቤን ራውለንስ እንዲሁም ከውስጥና ከውጭ "አውርቶ-በልቶ አደር" የከሰሩ ፖለቲከኞች በስተቀር፡፡

ኢህአዴግ እንከን የለሽ እንደሆነ እየመሰከርኩለትም አይደለም፡፡ ስራው ይመሰክርለታልና፡፡ ያም ቢሆን መላዕክቶች የመሠረቱት ፓርቲ ስላልሆነ ጉድለቶች ሊኖሩት እንደሚችሉ እገምታለሁ፡፡

ይሁንና በየትኛውም መስፈርት ቢመዘን ኢህአዴግ ተኪ የለውም– በዘመኑ፡፡ እናም ከኢህአዴግ ጐን ተገዳድረው፣ነገር ግን በአቅሙ- ቢስነታቸው ተሸማቀው በራሳቸው ጊዜ ከፖለቲካ ጨዋታው የተሰናበቱትን ሁሉ የፖለቲካ ሜዳው እንደጠበባቸው አድርጐ ማምታታቱ ከአንድ "ተመራማሪ" የሚጠበቅ አይመስለኝም፡፡

የሚስተር ራውለንስ "የፖለቲካው ሜዳ ጠበበ" ጨዋታ "የእናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ" ዓይነት ነገር ነች። እናም የምታዋጣው አደለችም፡፡

ስለሆነም ባህር ማዶ ተቀምጠው "ሻምፖኝ" እየተራጩ አድረው ማለዳ ላይ ኢትዮጵያን የሚያሙ ሁሉ ፖለቲከኞች አለመሆናቸውን ከአክራሪ ኒዮ-ሊበራሊዝም የውሻንብር ግርዶሽ ወጥቶ መረዳት ያስፈልጋል። እነዚህ ወገኖች "ቦተሊከኞች ናቸው"– እናቴ እንደምትለው፡፡

በእርግጥ ቤን ራውለንስ የፖለቲካ ምዕዳሩ እንዳልጠበበ ይገባዋል– አውቆ የዲታውን ጆርጅ ሶሮስ ረብጣ ዶላር ተከናንቦ ስለተኛ እንጂ። እናም ቢያንስ አባወራነትን የማይመጥኑ ፖለቲከኞችን ወግኖ መከራከሩ ግራ ቢያጋባው ነው፤ አቅመ ቢስ ምክንያቶችን የሚለቃቅመው፡፡ ነገሩ "የቸገረው እርጉዝ ያገባል" እንዲሉት ዓይነት መሆኑም አይደል?...

…እስቲ በምናብም ቢሆን ከሰውዬው ጋር ጥቂት ላውጋ፡፡ ማን ነበር ስምህ?- አዎ ቤን ራውለንስ ብለኸኛል፡፡ ደግሞም አቶ መለስ ከሌሉ ኢትዮጵያ የገና ዳቦ እንደምትሆንም ተገለጦልሃል፡፡ ድንቅ መገለጥ ነው፡፡

መቼም ነገን መተንበይ ነብይነት እንጅ ጥንቆላ ሊሆን አይችልም፡፡ ምንኛ አንጀት የምትበላ ምሁርነት ናት ጃል፡፡ ግና የመለስን ሞት እንደምን ከሀገር መበታተን ጋር እንዳዛመድከው የበርኒንግሃም ውቃቢ አምላክህ ትወቅ።

የግለሰብ መሞት ከሃገር መፍረስ ጋር መያያዙ የምር ያስፈራል፡፡ እርግጥ ነው ቤን ራውለንስ እንደ መሰከረው አቶ መለስ ታላቅ ፍጡር ናቸው—ወደር የሌላቸው የአፍሪካ ልጅ፡፡ የእርሳቸው ሞት ግን ሀገርን አይገድልም፡፡

አቶ መለስ እንጂ ጥለውት የሄዱት የፖርቲያቸው ርዕዮት- ዓለም አሁንም አለ፡፡ ነባሪያዊም ነው። ኢህአዴግም ሆነ ኢትዮጵያ አልተበታተኑም፤ መቼም አይበታተኑምም፡፡

ሚስተር ራውለንስ እኛ ኢትዮጵያውያን እኮ በአማተር መሃንዲስ የተደረደርን የእንቧይ ካቦች አይደለንም። በባህላችንም ሆነ በታሪካችን በሹም ሽር ምክንያት የተበታተንበት ጊዜ የለም፡፡ ምናልባትም

የዓለም ባንክን በወረፈበት ዘገባው በግልጽ እንዳስቀመጠው ታላቁ መሪያችንን የተካው አዲሱ አመራር የልማት ኘሮግራሞችን እንዳለ ለማስቀጠል መወሰኑ አበሳጭቶታል። ምኞቱም እቅዳችንን እንድንቀንስ አሊያም እንድናቆም ነው—“ባልበላውም ጭሬ በትነዋለሁ” እንዳለችው ዶሮ ዓይነት መሆኑ ነው።

እንደገባኝ ከሆነ የታላቁ መሪያችንን ዳና ተከትለን በሰፊው ልማትን ማቀዳችን ለቤን ራውለንስ አግባብነት የለውም። ልማትን እንዳናባክን ተመኝቷል ማለት ነው፡፡ ምናልባትም አዝኖልን መሆን አለበት፡፡ ትክክል ነው፡፡

እንደ እርሱ እሳቤ ማንበብና መፃፍ ከቻልን ዲግሪ ምን ያደርግልናል?— እናም የዩኒቨርስቲ ጋጋታ አያስፈልገንም፡፡ በእርሱ ቤት ታላቁ የህዳሴ ግድብም መሰረዝ አለበት፡፡ ሰውዬው እያለን ያለው እንደዚያ ነው፡፡ ምንኛ ፀረ-ኢትዩጵያዊነት ነው ጃል!…

የሰውዬው ፀረ-ኢትዩጵያዊነት የሚቀጥለው በኢትዮጵያ የተሰማሩ ዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶችን በመወረፍ ነው። ሚስተር ራውለንስ በሀገራችን የሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍ የልማት አጋሮችን /DAG/ የሰብአዊ መብት ጥሰት መኖሩን እንዲያምኑ፣ አምነውም በአደባባይ እንዲያወግዙ በጡት አባቱ “ሂዩማን ራይትስ ዎች” በኩል አስጠይቋቸው ነበር– ምልጃ መሆኑ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የልማት አጋሮቻችን ተጨባጭ ማስረጃ ባለማግኘታቸው አልተስማሙም– በዘገባው እንደጠቆመው። እውነትን በመናገራቸውና የእርሱ የቅጥፈት አባሪ ተባባሪ ባለመሆናቸው እንደ ከሃዲ ቆጥሮአቸዋል፡፡ ባለመዋሸታቸው ዋሾ እያላቸው መሆኑ ነው፡፡

ሚስተር ራውለንስ በስመ የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪነት ያነሳው ሌላኛው ጉዳይ አሸባሪነትንና አሸባሪዎችን የመከላከል አራምባና ቆቦ ዲስኩር ነው። እርግጥ እዚህ ላይ  አንድ የማይታበል ሃቅ አለ፡፡

ይኸውም በጋዜጠኝነት ስም ሁለት ቆብ ደፍቶ የሚነግድ የሽብር ተባባሪ ወንጀለኛን መንግስት ተጠያቂ ማድረጉ አይካድም፡፡ እናም በማረሚያ ቤት የሚገኙ ግለሰቦች እንዳሉ ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ እጥፊዎችን ለህግ ማቅረብ መንግስትን የሚያስወቅስ ሣይሆን የሚያስመሰግን ተግባር ይመስለኛል፡፡ ህገ-መንግስታዊ ግዴታም ስላለበት ህግና ሥርዓትን ማስከበሩ የግድ ነው፡፡ እናም እንደ ማንኛውም ሀገር ኢትዮጵያም ወንጀለኛን መቅጣቷ ለቤን ራውለንስ ለምን እንግዳ እንደሆነበት ግልፅ አይደለም፡፡

አሜሪካ ዊሊያም አሳንጅን ማሳደዷ ለምን አልገረመውም? ፣ ለምንስ በዊኪሊክስ ድረ-ገፅ ይፋ የሆነው የአሜሪካ መከላከያ ሰራዊት አባላት ኢራቅ ላይ ጋዜጠኞችን በጅምላ ግድያ መፍጀታቸው ለምን አልደነቀውም?... ወዘተርፈ.....

ያም ሆነ ይህ ግን፣ እርሱ ያለጥፋታቸው እንደታሰሩ አድርጐ የሚከራከላቸው ጋዜጠኞች ራሳቸው ጥፋተኝነታቸውን በይፋ ያመኑ እንዲሁም ፍርድ ቤት ቀርበው አሳማኝ ማስረጃ  ማቅለብ ያልቻሉ ናቸው፡፡

ከዚህ አንፃር በቅርቡ ምህረት የተደረገላቸው ሁለቱን ስዊድናውያንና በሰላማዊ ፓርቲ ስም ተደራጅቶ በሽብር ተግባር ወንጀለኛ መሆኑ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት አንዱዓለም አራጌን  መጥቀስ ብቻ በቂ ይመስለኛል፡፡

ሚስተር ላውረንስ እዚህም እዚያም በሚረግጠው ዘገባው ብዙ ብሏል፡፡ ግና እርስ በእርሱ የሚጣረስ ነው። በአንድ በኩል በመለስ አስተዋይነትና ታላቅነት አምኖ በዕቅዶቻቸውም ስኬት ፅኑ እምነት እንደለው ገልጿል፡፡

ብዙም ሳይዘገይ ደግሞ  መለስን ባወደሰበት ምላሱ ወቀሳውን ያስከትላል– የዕድገትና ትራንስፎርሚሽን ዕቅዱ የማይሳካ  በመሆኑ መከለስ እንዳለበት ምስኪን ምክር ቢጤም አክሏል፡፡ ድሆች ስለሆንን ምኞት እንዳይበዛብንና ብልጽግና እንዳያቅረን አዝኖልን ይመስለኛል፡፡ “አሳቢ አታሳጣን” ማለት ይኼኔ ነው። ቂ.ቂ.ቂ…

እዚህ ላይ ግን ልብ ልንለው የሚገባን ጉዳይ አለ። እርሱም የአክራሪው ተቋም መደበኛ ታምቡር ደላቂውና አሳዳሪው ድርጅት “ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም” እያሉን መሆኑ ነው፡፡

ምክንያቱም ያደገ በመሠረተ- ልማት፣ በትምህርትና በዴሞክራሲያዊ ስርዓት በማደግ ላይ ያለ ህዝብ ሐብቱን ያለ አግባብ ስለማያስመዘብር ማወቅ፣ መለወጥና ማደጋችን አይመቻቸውም፡፡ አይመቻቸውም ብቻም ሣይሆን አይፈልጉትም፡፡

እናም ሚስተር ራውለንስ በ“ሂውማን ራይትስ ዎች” ጥላ ስር ሆኖ የበሬ ወለደ ትረካን የሚያቀነቅነውም ከዚህ ማንነቱ በመነሳት ነው— የአክራሪ ኒዮ-ሊበራሊዝምን ፖለቲካዊ- ኢኮኖሚ ለማስረጽ፡፡ፍላጎቱም እንደ ቻይና እና ህንድ በድህነት ላይ ድል እንዳንቀዳጅ ነው፡፡

የአክራሪው ተቋም ባልደረባ በአስገራሚ ሁኔታ ከደቡብ ኦሞ ወደ ኬንያ የሚደረገውን የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታንም አውግዟል። እናም በእርሱ ሸውራራ ዕይታ የዓለም ባንክም ይሁን የአፍሪካ ልማት ባንክ ኢትዮጵያን ማገዛቸው ወንጀል ነው፡፡ የኦሞ ወንዝ የኬንያው ቱርካና ሃይቅ ገባር በመሆኑ ግድቡ ሃይቁን እንደሚጐዳው ለማስተማርም ይሞክራል፡፡

በእርሱ እሳቤ ኢትዮጵያና ኬንያ በመስኩ ምንም ዕውቀት የሌላቸው ጅል ህዝቦች መሆናቸው ነው፡፡ በመሠረቱ ሁለቱ ሃገሮች ይህን ታላቅ የሃይል መሥመር በመዘርጋት የሁለትዮሽ ተጠቃሚነታቸውን ሲወጥኑና ብሎም የአፍሪካ ልማት ባንክም ለዚሁ ኘሮጀክት ማፈፀሚያ ከፍተኛ ገንዘብ ሲፈቅድ በዘፈቀደ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡

አሉታዊ ጐኑ እርሱ "በእኔ አውቅላችኋለሁ" እንደደሰኮረው ቢሆን ኖሮ፣ ኬንያውያንም ሆኑ ኢትዮጵያውያን ዝም ባላሉ ነበር፡፡

በእኔ እምነት የቤን ራውለንስ ስጋት በመረጃ ላይ ያልተመሰረተ ከመሆኑም በላይ አፍሪካውያን ከተባበሩ ያድጋሉ፣ ካደጉ ደግሞ የኒዮ-ሊበራሊስቶች ተመጽዋች ስለማይሆኑ እንደልባችን ልናሽከረክራቸውና ልንጠቀምባቸው አንችልም ከሚል እሳቤ የመነጨ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ለእኛ ለኢትዮጵያዊና ለወንድሞቻችን ኬንያውያን ያለውን ንቀት የሚያሳይ ማን አለብኝነት ነው። ውድ ራውለንስ ሆይ! መቼም ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነውና የሁለቱን ሀገሮች ህዝቦች ወክሎ መናገር ከመሳለቂያነት የዘለለ ትርፍ ላንተም ይሁን ለተቋምህ የሚያመጣልህ ባለመሆኑ በመልማት ላይ ያሉትን ሀገራት ለቀቅ ማድረግ ማለፊያ ይመስለኛል ፡፡

ከመሰንበቻው በሲጋሽ ድርጅቶች ተቋማት ሰናይ ምግባር አዘንኩ እያለ ያለው ሌላኛው ግለሰብ አቶ ዳንኤል በቀለ ይሰኛል፡፡ ይስ ሰው የሂዩማን ራይትስ ዎች የምስራቅ አፍሪካ ወኪሌ ነው ብሎ የሾመው ባለሟሉ መሆኑ ይታወቃል።

"ሞትስ ድሮ ቀረ" እንደሚል ጨለምተኛ ፍጡር ግለሰቡ ዛሬ መለያውን ቀይሮ የኢትዮጵያ ወዳጆችን አብጠልጣይ ሆኖ ቢመጣም፣ ድሮም የክርስቲያናዊ ተራድኦ በጐ አድራጐት ድርጅት ስም ሲነግድ የነበረ የነውጠኛው ቅንጅት አመራሮች ጋሻ ጃግሬ ሆኖ አመፅን በመደገፍ በተራድኦ ስም የመጣውን ገንዘብ ድንጋይ ማስወርወሪያ ሲያርድግ የነበረ ነው፡፡

ታዲያ ግለሰቡ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አሉታዊ ገጽታዎችን ሁሉ ካሉበት በባትሪ እየፈለገ በል ሲለው ደግሞ እየፈበረከ በተቋሙ ስምና በ"ብሎጉ" የሚያሰራጭ ምግባረ እኩይ ሆኖ ብቅ ብሏል፡፡ እናም የተለመደ ምግባሩን እንጂ አዲስ ተአምር ስላላመጣ የሚገርም አይደለም፡፡

እናም ነገረ ስራው "ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም" እንዲሉት ዓይነት እንዲሁም ድርጊቱ ቀሽም ብቀላ በመሆኑ ለእርሱ ዝባዝንኬ እንካ ሰላንቲያ ምላሽ በመስጠት የአንባቢዎቼን ጊዜ መሻማት አልፈልግም። ለምን ቢሉ የተለመደ ምግባሩን እንጂ አዲስ ተዓምር ባለማውራቱ ነው።

ያም ሆነ ይህ ግን ፤ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነኝ ባዩ ቤን ራውለንስም ይሁን የመንፈስ ወንድሙ ዳንኤል በቀለ እንደሚያሟርቱት ኢትዮጵያ እንደዘበት የምትናድ የእንቧይ ካብ አይደለችም፡፡ አልነበረችምም፡፡

እኛ ኢትዮጵያዊያን የወሬ ማዕበል እንዳሻው የሚያንገላውደው ቅጥ አልባ ባህር አይደለንም፡፡ ማንም ያሻውን መለገፍ ይችላል።

እርግጥ ውሸት የቱንም ያህል ቢከመር ያው ውሸት ነው። እንትት የሻይ ማንኪያ ታህል ሃቅ ስለማይወጣው ከመጤፍ የምንቆጥረው አይደለም፡፡

ምክንያቱም ተራ የአሉባልታ ብዕር የሚፈታው ተራ ትውልድ በአዲሷ ኢትዩጵ ከቶም ሊኖር አይችልምና፡፡ ኢትዩጵያዊያን ዘመኑ የሥራ መሆኑን ስለሚያውቁ፤ ጦር ከፈታው የውሸት ብዕር የፈታው ዓይነት አሮጌ ተረት የሚያስደንቀን አይደለንም፡፡

“ምግባር ከምላስ፣ ተግባርም ከቃል በላይ” መሆኑን ጠንቅቀን እናውቃለን። የምናምነው የምናየውን እንጂ በበሉበት የሚጮሁትን እንደ ሚስተር ራውለንስና የገዛ ሀገሩን ጥቅሞች የሚፃረረው እንደ ዳንኤል በቀለ ዓይነት ግለሰቦችን አይደለም። እናም በበኩሌ “አልሰሜን ግባ በለው” ልላቸው እፈልጋለሁ።

ኢህአዴግ ያሳመነን ብዙ ስላወራ አይመስለኝም– ብዙ ስለሰራ እንጂ። ኢትዮጵያና አፍሪካ ለታላቁ መሪያችን ያነቡትና ያዘኑት አቶ መለስ በምግባራቸው ሠርተው በማሳየታቸው እንጂ ጠዋት ማታ ስላወሩ አይደለም፡፡

የዓለም አቀፍ ማህበረሰብም ይሁን ለጋሽ ድርጅቶች ሊደግፉንና ሊያግዙን የተነሱት ሁኔታዎች ከተመቻቹልን፣ የገንዘብ አቅማችን ካደገ ለመለወጥና ለማደግ የምንፈልግ ብሎም እንደምንችል በተግባርም ሰርተን በማሳየታችን ነው፡፡

እኔ አበቃሁ፡፡ ግና የቤተ-ክርስቲያን ስዕለት ያለበት ይመስል ፀረ-ኢትዩጵያዊነትን ማነብነብ የማይሰለቸው “ሂዩማን ራይትስ ዎች” ሌሎች አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሟርተኞች በሰብዓዊ መብት ስም የሌለ ድርሳናቸውን ከትበው አሉባልታቸውን እንደሚቀጥሉ ግልፅ ነው፡፡ እኛ ግን እውነታውን ከማደናገሪያው፣ ፍሬውን ከገለባው እየለየን በጀመርነው የዕድገት ጎዳና መጓዛችን አይቀሬ ነው፡፡ ቸር እንሰንብት።